# የሀገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ንቅናቄ

ኢትዮጵያ የኢትዮጵያዊያኖች ሳትሆን፤ የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መሬት ናት አሉን። ኢትዮጵያዊ የሚባል የጋራ ማንነት የለም አሉን። እውቅና የሚሰጠን በኢትዮጵያዊነት ሳይሆን በክልላዊነት ነው አሉን። የእኛ ልዕለ-ግብ የጨቋኝ እና የአምባገነን ሥርዓትን ለመለወጥ ነው። ዓላማችን ከጎሳ ፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ወደ የሁሉም ዜጎች እኩልነትና የህግ በላይነት የሚከበርባት፣የሥልጣን ምንጩ የሕዝብ የሚሆንባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚጥር የአገር-አድን ትግል ነው። በአሁኑ የአገር ማዳን ዘመቻ ወቅት ትኩረታችን ለሚቀጥለው ምርጫ ሳይሆን ለሚቀጥለው ትውልድ ነው። ዓላማችን ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዲሞክራሲ የሆነውን የጎሰኛ እና የጥላቻ ከፋፋይ ርዕዮተ-ዓለም በኢትዮጵያዊነት እሴቶች ለመተካት ነው። የኢትዮጵያዊነት ወረርሽኝ ማእበል እንዲሰራጭ መጣር ያስፈልገናል።

ዓላማችን ኢትዮጵያ ጥበብ የሞላበት ጉልበት እንድትሆን ነው! ጥረታችን እውቀት-መር ኢኮኖሚ ለመገንባት ነው። የኢትዮድያዊነት ርዕሰ-ግብ የአሁኑን የማፊያ ኢኮኖሚ እና የክልላዊ አፓርታይድ አምባገነን ስርዓት እንዳይቀጥል ለማድረግ ነው። ብዙ ሆነን አንድ የሚያደርገን ኢትዮጵያዊነታችን ነው። ለኢትዮጵያውያን ልዩነታችን ጌጣችን፤ አንድነታችን ኃይላችን ነው።

ገዢው ቡድን ለጎሳ መብትና እኩልነት ቆሜአለሁ እያለ ጎሳ ከጎሳ ጋር እየተጋጨ አንዲኖር እያደረገ፣ በኢትዮጵያዊ ዜግነት ጠንካራ አገራዊ ስሜት እንዳይኖር የሚያደርግ የውጭ ተልእኮውን በሚገባ የሚፈጽም የውጭ ባለ-አደራ መንግሥት ነው። ኢትዮጵያ የምትባል አገር ፈርሳ በምትኩ በክልላዊ መንግሥት ሥርዓት ትግሬ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሌ፣ አፋር፣ ሐረሬ...ወዘተ የሚባሉ የመንደር መንግሥታት (mini states) መስርቶ እርስ በእርሳቸው ሲዋጉ እንዲኖሩ ቀምሮ የተነሳ አገር-በቀል ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድን ነው።

አገር ወዳዱና ለውጥ ፈላጊው ኢትዮጵያዊ ያለው ምርጫ በጎሳ መለያየቱን ትቶ ተባብሮ በመደራጀት ሕዝባዊ እምቢተኝነትን በማፋፋም በአንድ አገር ዜግነት መቆምና ያለውን የጎሳ ፖለቲካ እና የአምባገነን ስርዓት የሚያስወገድ ስር-ነቀል ለውጥ ማምጣት ነው።

አባተ ካሣ